# የነዳጅ ውጤቶች የሥርጭት፣ የርክክብና የሽያጭ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 904/2014

Petroleum Products Distribution, Delivery and Sales Performance Directive No. 904/2014

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry of Trade and Regional Integration

ሰኔ 8፥ 2014

የፌዴሪል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) መሰረት የንግድና ቀጠናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የነዳጅ ውጤቶች የሥርጭት፣ የርክክብና የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 904/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1/ "የነዳጅ ውጤት" ማለት ከተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅ እና ከፔትሮሊየም ጋዝ፣ ባዮ-ፊውል ወይም ሴንተቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀናበር የተገኘ ንፁህ ወይም አግባብ ባለው መንገድ የተደባለቀ የነዳጅ ውጤት ሆኖ ቤንዚንን፣ ኬሮሲንን፣ ናፍጣን፣ ቀላልና ከባድ ጥቁር ናፍጣንና የአውሮፕላን ነዳጅን ያካትታል፣

2/ "የግብይት ተሣታፊ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን የሚያስመጣ፣ የሚያጣራ፣ የሚያደባልቅ፣ የሚያከማች፣ የሚያከፋፍል፣ የሚቸረችር፣ የሚያጓጉዝ፣ የሚልክ እና መሰል ተግባራትን እንዲያከናውን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

3/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት ነዳጅና የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ለማከናወን የተቋምና የሙያ ብቃትን በማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነዉ፤

4/ "ባለሥልጣን" ማለት የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ነው፡፡

5/ "ኩባንያ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በጅምላ በመግዛት ለማደያዎች እና ለቀጥታ ተጠቃሚዎች ለማሠራጨት ህጋዊ የሥራ ፈቃድ ያለው ነው፡፡

6/ "ድርጅት'' ማለት የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ነዉ፡፡

7/ "የነዳጅ አዳይ" ማለት ነዳጅን ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ ገዝቶ ለተጠቃሚውና ነዳጅ ማደያ በሌለባቸው ከተማና አካባቢዎች በችርቻሮ ለሚቸረችር ሰው የሚሸጥ ነው፡፡

8/ "ርክክብ" ማለት ከወደብና ከዴፖ የተጫኑ የነዳጅ ውጤቶችን በማደያ ላይ በአጓጓዡና በነዳጅ አዳዩ መካከል የሚደረግ የርክክብ ሥርዓት ነው፡፡

9/ "ማጓጓዣ" ማለት የነዳጅ ውጤቶችን ከወደብና ከዴፖዎች በመጫን ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚያጓጉዝ የነዳጅ ቦቴ ነው፡፡

## አንቀጽ 3 የመመሪያው አስፈላጊነት

በነዳጅ የግብይት ሰንሰለት ግልፅነት ያለው፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፣ የነዳጅ ትራንስፖርትና የርክክብ ሥርዓት በመዘርጋት፣ የምርቶቹን ተደራሽነትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ አስፈለጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## አንቀጽ 4 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ከወደብ እስከ ነዳጅ ማደያዎች ድረስ ባለው የሥርጭት፣የርክክብና የሽያጭ ሂደት ላይ ተሳታፊ በሆኑና የቁጥጥር ሚና ባላቸው አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 5 የባለሥልጣኑ ተግባራት

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1/ የነዳጅ ሥርጭትና ርክክብ መመሪያን ተግባራዊነት በተመለከተ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የሚሠሩ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣

2/ ነዳጅ ለመጫን ወደ ሥምሪት የሚገቡትን የማጓጓዣዎችና የማደያዎችን መረጃ ከኩባንያዎች በመቀበል ለድርጅቱ ያስተላልፋል ፣ አፈጸጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

3/ ማጓጓዣዎቹ በተሰጣቸው የሥምሪት መዳረሻ በሆነው የነዳጅ ማደያ ደርሰው ማራገፋቸውንና ህጋዊ ርክክብ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በጉዞ ላይ እያለ በማስቆም መረጃ የማጣራትና ከመስመር/መዳረሻ ዉጭ ሲጓዝ የተገኘውን የነዳጅ ተሽከርካሪን በህግ ቁጥጥር ሥር እንድውል ያደርጋል፣

4/ ከጅቡቲ ወደብና ከማሰራጫ ዴፖዎች የተጫነው የነዳጅ ውጤት በመረካከቢያ ሰነድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ የነዳጅ ኩባንያዎችና ማደያዎች ሥራ ላይ እንዲያውሉት ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

5/ በዘርፉ ያሉ የግብይት ተዋናዮች የተሰጣቸውን ተግባራት በተገቢው ሁኔታ መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

6/ ዕለታዊ የነዳጅ ውጤቶች የጭነት መረጃ በሲስተም በማደራጀት በክልሎች፣በከተሞችና በማደያዎች መካከል ተደራሽነትና ፍትሐዊነት መኖሩን ይከታተላል፣ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣

7/ በአሳማኝ ምክንያቶች ላይ ተመስርተው የሚቀርቡ የመዳረሻ ለውጥ ጥያቄዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ተገቢው ፈቃድ ሳይሰጣቸው ስምሪት ለውጥ በሚያደርጉ ኩባንያዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

8/ የነዳጅ መስፈሪያ ዲስፔንሰርና መለኪያዎች በየዓመቱ ካሊብሬት/በትክክል መስራታቸውን በማረጋገጥ/ ተደርገው ስለትክክለኛነቱ የሚገልጽ እስቲከር መለጠፋቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

## አንቀጽ 6 የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የንግድ ቢሮዎች ኃላፊነት

1/ በክልል እና በከተማ መስተዳድር ውስጥ ለሚገኙ የነዳጅ ማደያዎች በየቀኑ የሚላኩትን የነዳጅ ውጤቶች መረጃ ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በመቀበል በተዋረድ ላሉት የንግድ ቢሮ አካላትና የነዳጅ ማደያዎች ያስተላልፋል፣

2/ ነዳጅ ለተላከለት የነዳጅ ማደያ መድረሱንና መራገፉን ያረጋግጣል፣ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ህጋዊ መረካከቢያ ሰነድ አማካይነት ርክክብ እንዲፈጸም ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣

3/ የዞን ንግድ መምሪያዎች እና የወረዳ ንግድ ጽ/ቤቶች ክትትልና ቁጥጥር እንዲያድርጉ ያስተባብራል፤ በትክክል መፈጸሙን ያረጋግጣል፣

4/ ከዞን፣ ከወረዳዎችና ከከተማ መስተዳድሮች የነዳጅ አቅርቦትና ሥርጭትን የተመለከቱ ሪፖርቶችን አደራጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ና ለባለሥልጣኑ ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ 7 የዞን ንግድ መምሪያ የሥራ ኃላፊነት

1/ ከክልል ንግድ ቢሮ የሚላክለትን ዕለታዊ የነዳጅ ስርጭት መረጃ በሥሩ ለሚገኙ ወረዳዎችና ከተሞች ያሰራጫል፤ በመረጃው መሠረት ነዳጁ በተመደበላቸው ማደያዎች ስለመድረሱና ተገቢው ርክክብ ስለመፈጸሙ በሚላክለት ዕለታዊ የርክክብ ሪፖርት መሠረት ክትትል ያደርጋል፤ ወረዳዎችንና ከተሞችን ያስተባብራል፣

2/ በተመደበለት ከተማና ነዳጅ ማደያ በወቅቱ ያልደረሰ ወይም ሳይደርስ የቀረ የነዳጅ ቦቴን በተመለከተ ተገቢው ክትትል እንዲደረግ ለክልሉ የንግድ ቢሮ ከዝርዝር መረጃ ጋር ያሳውቃል፤

3/ ነዳጅ ማደያዎች የተራገፈውን ነዳጅ ለተጠቃሚው በትክክል እየተሸጠ መሆኑንና እንዳስፈላጊነቱ ማደያ በሌለባቸው ከተማዎችና አካባቢዎች በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት

እየተከፋፈለ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በወረዳዎችና በከተሞች የሚደረገውን የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ በየወሩ ለክልል ንግድ ቢሮ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 8 የከተማ ወይም የወረዳ ንግድ ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊነት

1/ ነዳጅ አዳዩ የነዳጅ መረካከቢያ እና የሽያጭ ሰነዶችን አደራጅቶ መያዙን ይቆጣጠራል፣

2/ በከተማው ወይም በወረዳው የነዳጅ ሥርጭት፣ ርክክብና የሽያጭ አፈፃፀሙን የሚከታተል ባለሙያ በቋሚነት ይመድባል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

3/ የተመደበው ባለሙያ አስቀድሞ በሚደርሰው ዕለታዊ የጭነት መረጃ መሰረት ተገቢውን ክትትል በማድረግና በቦታው ላይ በመገኘት የተሟለጠ ርክክብ እንዲፈፀም ማድረግ አለበት፤

4/ ለማደያው የተላከው የነዳጅ ቦቴ በቦታው ደርሶ ከማራገፉ በፊት እሽጉ ያልተከፈተ መሆኑንና የተላከው የነዳጅ መጠን በትክክል መራገፉን በማረጋገጥ ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ባለው የመረካከቢያ መዝገብ ላይ እንዲመዘገብ በማድረግ በአሽከርካሪውና በነዳጅ አዳዩ መካከል ርክክብ መፈጸሙን ባለሙያው ማረጋገጥ አለበት፤ በባለሙያው የተፈረመበትና የወረዳው ንግድ ፅ/ቤት ማህተም የተደረገበት የርክክብ ማስረጃ ለሾፌሩና ለነዳጅ አዳዩ ይሰጣል፤

5/ በነዳጅ ማደያው የተራገፈው ነዳጅ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተወሰነው የችርቻሮ ዋጋ መሠረት ለተጠቃሚው እየተሸጠ መሆኑን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

6/ በነዳጅ ማደያ የተራገፈውና የተሸጠው የነዳጅ ዓይነትና መጠን በየወሩ ለዞኑ ንግድ ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል፣

7/ የነዳጅ መስፈሪያ ዲስፔንሰርና መለኪያዎች በየዓመቱ ካሊብሬት/በትክክል መስራታቸውን በማረጋገጥ/ ስለትክክለኛነቱ የሚገልጽ እስቲከር መለጠፍ አለባቸው፣

8/ በመመሪያው መሠረት በማይፈጽሙ አካላት ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

## አንቀጽ 9 የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ኃላፊነት

1/ ከባለሥልጣኑ በሚላክለት የነዳጅ ማደያዎችና የማጓጓዣ ቦቴዎች መረጃ መሠረት የነዳጅ ሽያጭና የጭነት አገልግሎት ከተሟላ የጉዞ ሰነዶች ጋር ይሰጣል፣

2/ የነዳጅ ቦቴዎች ከወደብ ወይም ከአገር ውስጥ ዴፖዎች ነዳጅ ጭነው ከመውጣታቸው በፊት የነዳጅ ተረካቢ መዳረሻ የሚያመላክት ክልል፣ከተማ፣የነዳጅ ማደያውና የባለቤቱ ስም፣ የተሽከርካሪው ታርጋ ቁጥር፣ የጫነው የነዳጅ ዓይነትና መጠን፣የሾፌሩ ሥምና ስልክ ቁጥር እንዲሁም የነዳጅ የጭነት ሰነድ (FDC) ቁጥር የያዘ ጽሑፍ ከረዳት ሾፌሩ መቀመጫ ፊት ለፊት ባለው ሥፍራ መለጠፍ አለበት፣

3/ የየዕለቱን የነዳጅ ውጤቶች የሥርጭት መረጃ ለባለሥልጣኑና ለሚመለከታቸው አካላት በየቀኑ ያስተላልፋል፣

4/ በሚኒስቴሩ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ መሠረት ለጭነት የሚቀርቡ የነዳጅ ቦቴዎች የጂ.ፒ.ኤስ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው መሆኑን በማረጋገጥ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል

5/ ከወደብ ወይም ከሀገር ውስጥ ዴፖዎች ነዳጅ የጫነ ማጓጓዣ በተመደበለት መዳረሻ በማድረስ ነዳጁን ስለማራገፉና ተገቢውን ርክክብ ስለመፈፀሙ ከወረዳው ወይም ከከተማ አስተዳደሩ ንግድ ጽ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ሲያቀርብ ብቻ ለአሽከርካሪው ቀጣይ የጭነት አገልግሎት ይሰጣል፣

6/ ይህ መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወራት የዕፎይታ ጊዜ በኋላ የየኩባንያቸውን ዓርማ ወይም ምልክት ለጥፈው ለሚቀርቡ የነዳጅ ቦቴዎች ብቻ አገልግሎት ይሰጣል፡

7/ ከባለሥልጣኑ በሚሰጠው የፅሁፍ ውሳኔ መሠረት የታገዱ ኩባንያዎች፣ ማደያዎችና ተሽከርካሪዎች እንዳይስተናገዱ ያደርጋል፣

## አንቀጽ 10 የነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች ኃላፊነት

1/ ይህን መመሪያ ለማደያዎች፣ ለትራንስፖርት ማህበራትና ባለንብረቶችና ለአሽከርካሪዎች በማድረስ እንዲያዉቁትና እንዲተገብሩት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

2/ የመንገዱን ሁኔታ እና ርቀት በማገናዘብ አሽከርካሪው ከጭነት መነሻ እስከ መዳረሻው ድረስ የሚወስድበትን የጊዜ ገደብ ይወስናል፡፡ ለባለሥልጣኑና ለሚመለከታቸው ያሣውቃል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ዘግየተው በሚደርሱ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን የእረምት እርምጃ ይወስዳል፣

3/ ነዳጅ የጫነ አሽከርካሪ ማሽከርከር የሚችለው ከንጋቱ 10፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ብቻ መሆኑን ለአጓጓዡ በማሣወቅ ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኩባንያዎች በተገለፀው ገደብ ውሰጥ የየራሣቸውን የማሽከርከር የጊዜ ገደብ መወሰን ይችላሉ፤

5/ ኩባንየው የጭነት ስምሪት ለድርጅቱ ሲሰጥ ለባለሥልጣኑ በኢሜይል ወይም በኢንተርኔት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፣

6/ ነዳጅ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ተደራሽ እንዲሆን የእያንዳንዱን የነዳጅ ማደያ ፍላጐትና ወቅታዊ አቅርቦቱን ያገናዘበ ፍትሃዊ ስርጭት ማድረግ አለበት፣

7/ የነዳጅ አጓጓዥ ተሽከርካሪዎች ሥምሪት ሲሰጣቸውና ነዳጅ ጭነው ሲንቀሳቀሱ የተሟላ የጭነት ሰነድ መያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት፣

8/ ከወደብና ከሀገር ውስጥ ዴፖ የተጫነው ነዳጅ ለታዘዘለት ማደያ ወይም ሌላ መዳረሻ በትክክል መድረሱንና መራገፉን የመከታተልና የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፤ ይህንኑ ለባለሥልጣኑ በየቀኑ የማሳወቅ አለበት፣ ይህን ካልፈጸመ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፤

9/ ሚኒስቴሩ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የኩባንያውና ከኩባንያው ጋር ውል ገብተው የሚሠሩ የነዳጅ ቦቴዎች ጂፒኤስ እንዲገጥሙ ማድረግና መደገፍ አለበት፣

10/ በወደብ፣ በመንገድ ላይ እና በመዳረሻ ቦታዎች የነዳጅ ቦቴዎች ላይ አደጋ ሲከሰት መንስኤዉን በመለየት በ24 ሰዓት ዉስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፣

11/ በኩባንያዉ ወይም በግለሰብ የሚገነባው ማደያ የኩባንያዉን የደረጃና የደህንነት መስፈርቶችን አሟልቶ የተጠናቀቀ መሆኑን በማረጋገጥ ነዳጅ የማቅረብ ዉል መግባት አለባት፣

12/ የአሽከርካሪዎችን የሥራ አፈጻጸም የመከታተል፣የማብቃትና ጉድለት ባለባቸው ላይ እርምጃ የመውሰድ ሃላፊነት አለበት፣

13/ የቦቴ አሽከርካሪው አስቀድሞ የጫነው ነዳጅ እንዲያድርስ የታዘዘበት ማደያ ማድረሱንና ማራገፉን ሳያረጋገጥ ዳግም ስምሪት መስጠት የለበትም

14/ የእያንዳንዱን ማደያ፣ ተሽከርካሪና አሽከርካሪ ትክክለኛ መረጃ አደራጅቶ መያዝ አለበት፤

15/ የመዳረሻ ስምሪት ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልገው በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥና ማስረጃ በማያያዝ ባለሥልጣኑን ማስፈቀድ አለበት፣

16/ በተለያየ ምክንያት ከስምሪት የወጡ ተሽከርካሪዎችና ሥራ ያቆሙ ማደያዎች ሥራ ካቆሙበት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፣

17/ በነዳጅ ማደያዎች የተተከሉ የነዳጅ የመቅጃ ማሽኖችን የመጠገን እና ለማደያው ኦፕሬተርና ሠራተኞች ስለነዳጅ አያያዝና ደህንነት በተመለከተ ስልጠና መስጠት አለበት፣

18/በነዳጅ ግብይት ለመሣተፍ የተዘጋጁ አዳዲስ ተሽከርካሪዎችና ማደያዎች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ለባለሥልጣኑ ማሳወቅና ማስመዝገብ አለበት፣

19/ይህ መመሪያ በሚኒስቴሩ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት የስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የሚያስተዳድራቸው ቦቴዎች በሙሉ የኩባንያውን ዓርማ ወይም ምልክት ለጥፈው እንዲሰማሩ ያደርጋል፤

20/ ሥራ ባቆመና በጥገና ላይ ባለ የነዳጅ ማደያ ስም ነዳጅ መሸጥም ሆነ መጫን የለበትም፣

21/ በአንድ ማደያ ስም የተጫነን ነዳጅ ለሁለት ማደያዎች ማካፈል ካስፈለገ ከመነሻው በሁለቱም ማደያዎች ስም የጉዞ ሰነድ መዘጋጀት አለበት፤ ይህን ማድረግ ያልተቻለ እንደሆነ ቦቴው ከመድረሱ በፊት የሁለተኛውን ማደያ ሥም ለሚመለከታቸው አካላት ማሣወቅ አለበት፤

22/ ከወደብና ከዴፖ የተጫነው ነዳጅ በእያንዳንዱ ነዳጅ ማደያ ደርሶ በመረካከቢያ ሰነድ ርክክብ እንዲደረግ ማድረግ አለበት፣

23/ የነዳጅ ኩባንያዎች የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን በመጠቀም ግዥና ሽያጭ ማከናወን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 11 የነዳጅ አዳይ ኃላፊነት

1/ ከባለሥልጣኑ በሚሰጠው የርክክብ ቅፅ መሠረት የነዳጅ ርክክብ መዝገብ ያደረጃል፣ ሌሎች የነዳጅ ርክክብና የሽያጭ ሰነዶችን አሟልቶና አደራጅቶ መያዝ አለበት፣

2/ ነዳጅ የጫነ ተሽከርካሪ ከማደያው ሲደርስ የቦቴው እሽግ አለመከፈቱን በማረጋገጥ የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር የንግድ ጽ/ቤት ሠራተኛ በተገኘበት ከአሽከርካሪው ጋር ርክክብ ይፈፅማል፤ ስለመረከቡ በንግድ ጽ/ቤቱ ተወካይ የተረጋገጠ ማስረጃ ለአሽከርካሪው መስጠት አለበት፣

3/ በርክክብ ወቅት አሽከርካሪው በተቀመጠለት የመድረሻ ጊዜ ውስጥ መድረሱን በማረጋገጥና በመዝገቡ ላይ የተቀመጡትን መጠይቆች በሙሉ በትክክል በመሙላት አሽከርካሪውን ማስፈረም አለበት፣

4/ የነዳጅ አዳዩ በሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅ መዝገቡን የማቅረብና የማሣየት ግዴታ አለበት፣

5/ በነዳጅ መጠን መለኪያ ፍሎው ሜትር የተለካውና የቦቴው ካሊብሬሽን ከሚያሰየው መጠን ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱን አረጋግጦና መዝግቦ ለአሽከርካሪው መስጠት አለበት፣

6/ በቦቴው ካሊብሬሽን እና በፍሎው ሜትሩ መካከል የመጠን ልዩነት ካጋጠመ ልዩነቱ በኩባንያው፣ በትራንስፖርተሩ መካከል ባለው ውል መሰረት እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፣

7/ ነዳጅ አዳዩ በማደያው የነዳጅ መጠን መለኪያ ፍሎው ሜትር ማስገጠም አለበት፣

8/ የነዳጅ መጠን መለኪያ ፍሎው ሜትር በሁሉም የነዳጅ ማደያዎች ተገጥመው የሚጠናቀቅበት የጊዜ ገደብ በሚኒስቴሩ ይወሰናል፣

9/ የነዳጅ ማደያ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም አለበት፣ በቀጣይ አገልግሎት አሰጣጥን የሚያቀላጠፍ አውቶማቲክ የሽያጭ እና የደረሰኝ ማሽን ማስገጠምና መጠቀም አለበት፣

10/በነዳጅ ማደያው የተራገፈው የነዳጅ ዓይነትና መጠን አስመልክቶ በተረከበበት ዕለት በአካባቢው ለሚገኘው የንግድ ጽ/ቤት እና ለኩባንያው በጽሑፍ ሪፖርት ማድረግ አለበት፣

11/ማንኛውም ነዳጅ አዳይ የነዳጅ ውጤቶችን ሚኒስቴሩ በየጊዜው በሚወስነው የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ እና በሚወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ መሠረት መሸጥ አለበት፣ በሚኒስቴሩ ከተወሰነው ዋጋ በላይ በሚሸጥ የነዳጅ አዳይ ላይ የአካባቢው ንግድ ፅ/ቤት አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ መውሰድ አለበት፤

## አንቀጽ 12 የነዳጅ ቦቴ ባለንብረት ወይም የትራንስፖርት ማህበራት ኃላፊነት፣

1/ ይህንን መመሪያ ለአሽከርካሪዎች የማድረስ፣እንዲያውቁትና እንዲተገብሩት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

2/ ተሽከርካሪው ነዳጅን ለማጓጓዝ የሚያስችለው የካሊብሬሽንና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲኖረው ማድረግ አለበት፣

3/ ሚኒስቴሩ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በነዳጅ ቦቴዎች ላይ በኩባንያዉ መስፈርት መሠረት ጂፒኤስ ማስገጠም አለበት፣

4/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 5 እና 6 መሠረት ከነዳጅ አዳዩ ጋር የነዳጅ ርክክብ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

5/ አሽከርካሪው ሊኖረው የሚገባውን የሥራ ብቃትና ዲሲፒሊን ያሟላ መሆኑን እና ተጠያቂነትን ሊያረጋግጥ በሚያስችል አኳኋን ቅጥር መፈጸም አለበት፣

6/ የተሸከርካሪውን ስምሪት የመከታተልና ችግሮች ሲኖሩ በፍጥነት ማስተካከል አለባቸው፣

7/ የነዳጅ ውጤቶችን የማጓጓዝ ሂደቱ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት እንዳይስተጓጎል መከታተል አለበት፣

8/ የእያንዳንዱን ተሸከርካሪ እና አሽከርካሪ ሙሉ መረጃ አደራጅቶ መያዝ አለበት፣ ሲጠየቅም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ማቅረብ አለበት፣

9/ በነዳጅ ቦቴዎች ላይ ኩባንያዎች አርማቸውን ወይም ምልክታቸውን እንዲለጥፉ መተባበር አለበት፣

10/ በነዳጅ ቦቴዎች ላይ ከረዳት ውጭ ሌላ ሰው እና ህገወጥ ዕቃ እንዳይጭን ለአሽከርካሪው ማሳወቅ አለበት፣

11/ ነዳጅ የጫነ ቦቴ ከንጋቱ 10 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ብቻ እንዲጓዙ ማደረግ አለባቸው፡፡

12/ አሽከርካሪዎች የተሰጣቸውን ሥምሪት ተቀብለው እንዲፈፅሙ መከታተልና መቆጣጠር አለበት፤

13/ አሽከርካሪዎች ያለበቂ ምክንያት ነዳጅ ጭነው እንዳይቆሙ መከታተል አለበት፤

## አንቀጽ 13 የነዳጅ ቦቴ አሽከርካሪዎች ኃላፊነት

1/ ከወደብ ወይም ከሀገር ውሰጥ ዴፖ የተረከበውን ነዳጅ ለተጫነለት ማደያ ወይም መዳረሻ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውሰጥ በማድረስና የወረዳው ወይም የከተማው ንግድ ፅ/ቤት ሠራተኛ በተገኘበት በመረካከቢያ መዝገብ በማስመዝገብ ርክክብ መፈፀም አለበት፤ የርክክብ ሰነዶችን በጥንቃቄ በመያዝ ለሚመለከታቸው ይሰጣል፤

2/ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 5 እና 6 ላይ በተገለፀው አግባብ ከነዳጅ አዳዩ ጋር የነዳጅ ርክክብ ማድረግ አለበት፤

3/ በኩባንያው በኩል የስምሪት ለውጥ ሲያጋጥም ጥያቄው ለባለሥልጣኑ ቀርቦ ስለመፈቀዱ የጽሑፍ ማስረጃ ሳይደርሰው ነዳጁን ወደሌላ መዳረሻ መውሰድ የለበትም፣

4/ የነዳጅ ቦቴውን እሽግ ለተጫነለት የነዳጅ ማደያ ደርሶ በነዳጅ አዳዩና በንግድ ጽ/በት ሠራተኛው ታይቶና ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ እስኪፈታ ድረስ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፣

5/ የተሸከርካሪውን ስምሪት ለመቆጣጠር የሚገጠሙትን ጂፒኤስ እና ሌሎች መሣሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝ ግዴታ አለበት፣

6/ ነዳጅ ጭኖ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የተሟላ የጉዞ ሠነዶችን መያዝ አለበት፣

7/ በነዳጅ ቦቴዎች ላይ ከረዳት ውጭ ሌላ ሰው እና በህግ የተከለከሉ ዕቃዎችን መጫን የለበትም፣

8/ ኩባንያ በቦቴ ላይ የሾፌር ረዳትን የመጠቀም ሁኔታን በራሱ አሠራር ሊወስን ይችላል፣

9/ ነዳጅ የጫነ አሽከርካሪ የሥራ ሠዓት ከንጋቱ 10 ሰዓት እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ሲሆን ኩባንያው ይህንኑ ያገናዘበ የሥራ ሰዓት መወሰን ይችላል፤

10/ የነዳጅ ቦቴ አሽከርካሪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8 ላይ በተመለከተው የሥራ ሰዓት ወቅት ለመመገብና ለዕረፍት በአንድ ቦታ ከ2 ሰዓት በላይ መቆም የለበትም፡፡ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ ያለበቂ ምክንያት ቆሞ በተገኘ የቦቴ አሽከርካሪ ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፤

11/ አሽከርካሪው የጫነውን ነዳጅ በህገወጥ ተግባር ላይ ካዋለ በህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፣

12/ የጫነውን ነዳጅ ከተጫነለት መዳረሻ ውጭ በሌላ ማደያ ካራገፈ ከባለማደያው ጋር በጋራ፣ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፣አስተዳደራዊ እርምጃም ይወስዳል፣

13/ ነዳጅ ጭኖ በጉዞ ላይ እያለ በተቆጣጣሪ አካላት የሚጠየቀውን መረጃ የመስጠት ወይም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 14 የነዳጅ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ኃላፊነት

1/ ባለሙያው ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከሚመለከተው የአከባቢ ፖሊስ እና የፍትህ አካላት ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፣

2/ ባለሙያው ተቆጣጣሪ ስለመሆኑ የሚገልፅ የመስሪያ ቤት መታወቂያ ወረቀት እና የሥራ ትእዛዝ ደብዳቤ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት አካል ወይም ባለቤት ማሳየት አለበት፤

3/ በቁጥጥር ሥራ ወቅት የታየውን ጉድለት ለድርጅቱ ባለቤት ወይም ህጋዊ ተወካይ የማሳወቅ እና በቁጥጥር ወቅት በታዩ ግኝቶች ላይ መፈራረም አለባቸው፤

4/ ተቆጣጣሪው አካል ለቁጥጥር ሲወጣ የቁጥጥር ተግባራትን ከሚያስተባብረው ኃላፊ ጋር ስለሚቆጣጠረው ማደያ ወይም የነዳጅ ቦቴ ወይም ሌላ ተግባር እና በሚደረገው የቁጥጥር አካሄድ ላይ ስምምነት ያደርጋል፤

5/ ተቆጣጣሪው አካል ባደረገው ቁጥጥር ያገኘውን ውጤት በቼክ ሊሰት ላይ በመሙላት ቁጥጥር ከተደረገበት ድርጅት ጋር በመፈራረም ለሃላፊው ሪፖረት ያቀርባል፤

6/ ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥር ተግባሩ አስገዳጅ በሆነ ምክንያት ከመንግሥት የሥራ ስዓት ውጪ የሚያከናውን ከሆነ አግባብ ካለው ባለሥልጣን የትእዛዝ ደብዳቤ መያዝና ቁጥጥር ለሚደረግበት ድርጅት ማሳየት አለበት፡፡

**አንቀጽ 15 አስተዳደራዊ ቅጣት**

1/ ማንኛውም የነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያ እና አዳይ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ተግባራት በአግባቡ ያልፈጸመ እና መመሪያውን የጣሰ ሆኖ ሲገኝ እንደየጥፋቱ ክብደት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሮ ከአከፋፋይነት ከማገድ እስከ ፈቃድ መሠረዝ የሚያደርስ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

2/ ማንኛውም የነዳጅ ቦቴ ባለንብረት እና አሽከርካሪ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩትን ተግባራት በአግባቡ ያልፈጸመ እና መመሪያውን የጣሰ ሆኖ ሲገኝ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት ጀምሮ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ ሚኒቴር ጋር በመነጋገር የነዳጅ ጭነት ሥምሪት እና የአሽርካሪነት ፈቃዱን ከማገድ እስከ መሠረዝ የሚያደርስ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

3/ በየእርከኑ የቁጥጥር ሥራ እንዲሠራ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም አካል በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና በዚህ መመሪያ ላይ ከተዘረዘረው አሠራር ውጭ የቁጥጥር ሥራ ሲያከናውን የተገኘ አካል እንደየጥፋቱ ክብደት በዲሲፒሊን ሥርዓት ከመጠየቅ እስከ ከሥራ መባረር የሚያደርስ እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል እና በፍትሐ ብሔር ህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 16 የመተባበር ግዴታ**

ተቆጣጣሪው አካል ይህን መመሪያ በማስፈፀም ሂደት ሲጠየቁ የአከባቢው ፖሊስ እና የፍትህ አካላት የመተባባር ግዴታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 17 ተፈፃሚነት የሚኖራቸዉ ህጎች**

በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የወንጀል እና የፍትሐ-ብሔር ህጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 18 አስፈፃሚ አካላት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣን መ/ቤቱ በክልል እና በከተማ አስተዳደር፣ በዞን እና በወረዳ ንግድን በሚመሩ አካላት አማካይነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 19 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከሰኔ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አቶ ገብረ መስቀል ጫላ**

**የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር**

**አዲስ አበባ**